ጋዜጣዊ መግለጫ

አሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ
2013/09

ለተጨማሪ መረጃ በ011-130-7033 ይደውሉ
ድረ-ገጽ - http://ethiopia.usembassy.gov

የአሜሪካ መንግስት በሶማሌ ክልል የግመል ወተት ፕሮጀክት ይፋ አደረገ

አዲሱ ፕሮጀክት 50,000 ለሚደርሱ አነስተኛ አርብቶአደሮች ድጋፍ ያደርጋል

ሚያዝያ 17 ቀን 2005 ዓ.ም.፣ ጅጅጋ፣ ሶማሌ ክልል፡- የአሜሪካ መንግስት ፊድ ዘ ፊውቸር የሚባለው የፕሬዚደንቱ መርሃግብር አካል የሆነና ፣በአሜሪካ የዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ (ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ) በኩል የሚተገበር የግመል ወተት የእሴት ሰንሰለት ልማት ፕሮጀክት መጀመሩን በዛሬው ዕለት በሶማሌ ክልል ፋፋን መንደር በተደረገ ስነስርዓት ላይ ይፋ አደረገ፡፡ ፕሮጀክቱ በሶማሌ ክልል የግመል ወተት ተዋጽኦዎችን ምርት እና የገበያ ተወዳዳሪነት በማሻሻል ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ለመጨመርና 50,000 ለሚሆኑ በሲቲ (ሽንሌ) እና ፋፋን (ጅጅጋ) ዞኖች ለሚኖሩ ቤተሰቦች የተሻሻለ ምግብ ለማቅረብ ያስችላል፡፡

በፕሮጀክቱ ማብሰሪያ ስነስርዓት ላይ ንግግር ያደረጉት የሶማሌ ክልላዊ መንግስት ምክትል ፕሬዚደንት ክቡር አብዲፈታህ መሐሙድ ሀሰን፤ ‹‹የግመል ወተት የእሴት ሰንሰለት ልማት ፕሮጀክት ለአርብቶ አደሮች ባህላዊ ኃብት ተስማሚ ከመሆኑ ሌላ፣ ለኢትዮጵያ የግብርና ዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ነው፡፡›› ብለዋል፡፡

በአረጋውያንና ሕጻናት አርብቶአደሮች ማህበር የሚተገበረው ፕሮጀክት በግመል ወተት አመራረት ከግመሎቹ አንስቶ እስከ ገበያ ቦታ ድረስ ያለውን ሙሉ የእሴት ሰንሰለት ያሻሽላል፡፡ፕሮጀክቱ የግመልን ምርታማነት ለመጨመር በሚያስችል የምርጥ ዝርያ ልማት፣ የተሻሻለ የእንስሳት መኖ እና ድርቆሽ እንዲሁም በእንስሳት ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ፕሮጀክቱ ለማሕበረሰቡ አገልግሎት የሚሰጡ የእንስሳት ጤና ሰራተኞችን አቅም በመገንባት፤ የግመል በሽታዎችን እንዲመረምሩ እና ሕክምና እንዲሰጡ ማስቻል ላይ ልዩ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ፕሮጀክቱ ምርትን ለማሻሻል ለወተት አምራቾች እና አሰባሳቢዎች የወተት ጥራት እና ንጽሕናን መጠበቅ በሚቻልበት ዘዴ ላይ ስልጠና ከመስጠት ጎን ለጎን፤ ለግመል ወተት ተገቢውን ጥራትና ደረጃ ለማዘጋጀት ከሶማሌ ክልላዊ መንግስት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡ በመጨረሻም ፕሮጀክቱ ገበያውን ለማጠናከር በአካባቢው የሚገኙ የወተት ገበያዎችን ከወተት አምራቾች እና አቅራቢዎች፣ የንጽሕና ቁጥጥር እና የምግብ ደህንነት ደረጃዎች እንዲሁም ከመንገዣ ስርዓቶች ጋር ያስተሳስራል፡፡

በአሜሪካ የዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ (ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ)- የኢትዮጵያ ሚሽን ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር ባደረጉት ንግግር ‹‹ኢትዮጵያ የግመል ምርትን የአርብቶአደር ኑሮ ዋስትና እና ልማት ቁልፍ መሳሪያ በማድረግ ረገድ ግንባር ቀደም የመሆን ዕድል አላት፡፡ በሶማሌ ክልል ከሚታየው የአየር ንብረት መለዋወጥ አንጻር፤ ግመሎች የወደፊቱ አዋጭ እንስሳት ናቸው፡፡ ይህ ፕሮጀክት ስኬታማ እንደሚሆንም ተስፋ አለኝ፡፡›› ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቱ የተሻለ የቴክኒክ ዕውቀትና ተሞክሮ በማቅረብ፤ የወተትን ምርታማነት እና በገበያ ያለውን ተወዳዳሪነት ይጨምራል፤ ይህ ደግሞ የአነስተኛ አምራቾችን ምርታማነት፣ የምግብ ዋስትና እና ገቢ ያሻሽላል፡፡

###

USAID FROM THE AMERICAN PEOPLE